የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

፴፩ኛ ዓመት ቁጥር ፰
አዲስ አበባ ታህሳስ ፩ ቀን ፪ሺ፲፯

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

31th Year No. 8
ADDIS ABABA, 10th December, 2024

<u>ማውጫ</u>

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፶፩/፪ሺ፲፯

የፓሪስ ኢንዱስትሪያዊ ንብረት ኮንቬንሽን ማጽደቂያ አዋጅ ……........................ገጽ ፲፯ሺ፬፻፭

**<u>Content</u>**

Proclamation No. 1351/2024

The Paris Convention for the Protection of Industrial Property Ratification Proclamation ………..………………………........Page 17405

**አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፶፩/፪ሺ፲፯**

**<u>የፓሪስ ኢንዱስትሪያዊ ንብረት ኮንቬንሽንን ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ</u>**

በአባል ሀገራት መካከል ሕብረት በማቋቋም የኢንዱስትሪ ንብረትን ለመጠበቅ እ.ኤ.አ. መጋቢት ፳ ቀን ፩ሺ፰፻፹፫ የወጣው የፓሪስ ኢንዱስትሪያዊ ንብረት ጥበቃ ኮንቬንሽን ማጸደቅ አስፈላጊ በመሆኑ፤

ኮንቬንሽኑ ለአእምሯዊ ንብረት መብቶች ዓለም አቀፋዊ ደረጃዎችን ለማውጣት መሰረት በመሆኑ፤

ኮንቬንሽኑ የአባል ሀገራት የፈጠራ ባለቤቶች መብቶቻቸውን በሀገራችን ውስጥ በተቀላጠፈ ሁኔታ እንዲያስመዘግቡና እንዲያስጠብቁ በማስቻል ኢንቨስትመንትን ለመሳብ እንዲሁም የቴክኖሎጂ ሽግግርን ለማጠናከር የሚያግዝ በመሆኑ፤

**PROCLAMATION No. 1351/2024**

**<u>A PROCLAMATION TO RATIFY PARIS CONVENTION FOR THE PROTECTION OF INDUSTRIAL PROPERTY</u>**

**WHEREAS,** it is necessary to ratify the Paris Convention for the Protection of Industrial Property adopted on March 20, 1883 to protect industrial property by establishing a union between member countries;

**WHEREAS,** the Convention provides a foundation for the development of international standards for intellectual property rights;

**WHEREAS,** the Convention supports attraction of investment and strengthens technology transfer by enabling owners of inventions of member countries to efficiently register their rights in our country and get protection;

ኮንቬንሽኑ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙትን ፓተንቶችን፣ ግልጋሎት ሞዴሎችን፣ ኢንዱስትሪ ንድፎችን፣ ንግድ ምልክቶችን፣ አገልግሎት ምልክቶችን፣ ንግድ ስሞችን፣ ምንጭ አመልካቾችን ወይም መገኛ ምንጮችን በዓለም አቀፍ ደረጃ እንዲጠበቁ ለማድረግና ተገቢ ያልሆነ ውድድርን ለመከላከል የሚያስችል በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥቅምት ፳፮ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም ባካሄደው ፬ኛ መደበኛ ስብሰባ ያጸደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግስት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "የፓሪስ ኢንዱስትሪያዊ ንብረት ኮንቬንሽን ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፶፩/፪ሺ፲፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**፪. <u>የኮንቬንሽኑ መጽደቅ</u>**

እ.ኤ.አ. በመጋቢት ፳ ቀን ፩ሺ፰፻፹፫ በፓሪስ የወጣው በስቶክሆልም በሐምሌ ፲፬ ቀን ፩ሺ፱፻፷፯ ተከልሶ በመስከረም ፳፰ ቀን ፩ሺ፱፻፸፱ የተሻሻለው የፓሪስ ኢንዱስትሪያዊ ንብረት ጥበቃ ኮንቬንሽን በዚህ አዋጅ ጸድቋል፡፡

**፫. <u>ተፈጻሚ የማይሆን ድንጋጌ</u>**

፩/ የዚህ አዋጅ አንቀፅ ፪ ድንጋጌ ቢኖርም የኮንቬንሽኑ አንቀፅ ፳፰ ንኡስ አንቀፅ (፩) በኢትዮጵያ ላይ ተፈፃሚ አይሆንም፡፡

**WHEREAS**, the Convention helps patents, utility models, industrial designs, trademarks, service marks, trade names, indications of source or appellations of origin found in Ethiopia to have international protection and to prevent unfair competition;

**WHEREAS,** the House of Peopels' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Convention at its 4th Ordinary Session held on the 5th day of November 2024;

**NOW, therefore**, in accordance with Sub-Articles (1) and (12) of Article 55 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows.

**1. <u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as "the Paris Convention for the Protection of Industrial Property Ratification Proclamation No. 1351/2024".

**2. <u>Ratification of the Convention</u>**

The Paris Convention for the Protection of Industrial Property, adopted in Paris on March 20, in 1883, revised in Stockholm on July 14, 1967 and amended on September 28, 1979, is hereby ratified.

**3. <u>Inapplicable Provision</u>**

1/ Notwithstanding the provisions of Article 2 of this Proclamation, Sub-Article (1) of Article 28 of the Convention shall not apply to Ethiopia.

፪/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም የኢትዮጵያ መንግሥት በማንኛውም ጊዜ የኮንቬንሽኑ አንቀፅ ፳፰ ንኡስ አንቀፅ (፩) ተፈጻሚ እንዲሆን ሊወስን ይችላል፡፡

፬. <u>አስፈጻሚ አካል</u>

የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን የፓሪስ ኢንዱስትሪያዊ ንብረት ኮንቬንሽንን የማስፈጸም ኃላፊነት በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል፡፡

፭. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ታህሳስ ፩ ቀን ፪ሺ.፲፯ ዓ.ም**

**ታዬ አጽቀሥላሴ**
**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዘዳንት**

2/ Notwithstanding the provision of Sub-Article (1) of this Article, the Ethiopian Government may, at any time, decide the applicability of the provision of Sub-Article (1) of Article 28 of the Convention to Ethiopia.

**4. <u>Implementing Organ</u>**

The Ethiopian Intellectual Property Authority is hereby empowered to implement the Paris Convention for the Protection of Industrial Property.

**5. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall come into force upon publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, On this 10th day of December, 2024**

**TAYE ATSKE SELASSIE**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**